# ተወለደ እንጂ አልሞተም

*(ከዚህ ዓለም በሞት ለተለዩት ለታላቁ ሊቅ ለአለቃ አያሌው ታምሩ መታሰቢያ)*

(ኢንሰርሙ ሰይፈ ገብርኤል)

አያሌው የንጋት ኮከብ፣
የሊቃውንት ዓምባ ገደብ፣
የተዋሕዶ አንደበቷ፣
የትርጓሜ መስተዋቷ።
የክልዔ ባሕርይ መዶሻ፣
የኑፋቄ መርዝ ማርከሻ።
ከምድረ ጎዣም ፈንጥቀህ፣
በወንጌል ጸዳል በርተህ፣
እነሆ ሸዋ ጠለቅህ፣
አፈር መሬቷን ቀመስህ።

  አያሌው የንጋት ኮከብ፣
  የሊቃውንት ዓምባ ገደብ፣
  በጭራሽ አንተስ አልሞትክም፣
  ተወለድክ እንጂ ዳግም።

የሞተውስ ቅሉ ሌላ - መክሊቱን ከአፈር የቀበረ፣
ቀንበር ክህነቱን ሰብሮ - በእርፉ ወደኋላ የቆፈረ።
በጎች ምዕመናኑን በትኖ - ከቀበሮዎቹ ጋር ያበረ።
የጋጡን ግድግዳ ነድሎ - አውሬውን በቤቱ ያሳደረ።
ምን ይሆን አለቃ ምስጢሩ - በሱባዔዋ የማረፍህ፣
ኃላፊውን ዓለም ንቀህ - ከማይቀረው መጨመርህ?
በአባ ጊዮርጊስ ሰዓታት - ብትላት ንዒ ማርያም እምየ፣
እሷም ጸሎህን ሰምታ - አለችህ ‹‹ንዓ ወልድየ››፣
**ወይስ …**
‹‹ኢታርዕየኒ ሙስናሃ ለቤተ ክርስቲያን›› - ያልከው ጸሎትህ ተሰማ፣
የተሰናበትህ ከዚህች ዓለም - ባዲሱ ሺህ ዓመት ዋዜማ?
የቤተ ክርስቲያንን ዕጣ ፈንታ - አለቃ ንገረን ትንቢት፣

ደግ ቀን ይመጣ ይሆን - ወይስ ይብሳል ይኸው መዓት?

አያሌው የንጋት ኮከብ፣

የሊቃውንት ዓምባ ገደብ፣

እኔስ ሞተሃል አልልም፣

ተወለድህ እንጂ ዳግም፡፡

አለቃ አያለው ታምረኛ፣ - ስምህ መራህ ወደ ግብርህ፣

ተዋሕዶን አገነንካት - ታምሯን ለዓለም ነገርህ፡፡

እንግዲህስ ሩጫህ ተፈጸመ - እነሆ የድል አክሊልህ፣

ከሸዋው ጎርጎርዮስ ከጳጳሱ - ከአድማሱ ጀምበሬ ተደመርህ፣

ከአቡነ ጴጥሮስ ከሰማዕቱ - ከዶክተር አየለ ተሰለፍህ፡፡

ዕንባዬ አይፍሰስ አለቃ - አያሌው ሞተሃል አልልም፣

በእመቤታችን ትንሣኤ - አረፍክ እንጂ ለዘላለም፡፡

*ተጻፈ፡- የነሐሴ ኪዳነ ምሕረት ዋዜማ 1999 ዓ.ም*

*ሜሪላንድ (ሀገረ ማርያም) አሜሪካ*